# <u>ዳውን ዳውን ወያኔ !!</u>

*መስፍን ማሞ ተሰማ*



ከወልቃይት ኮንሶ ምነው አይታረስ
ከጋምቤላ ሐረር ምነው አይታረስ
በኦጋዴን ምድር ምነው አይታረስ
ሐራ ቢሾፍቱ ላይ ምነው አይታረስ
በሬሳ ላይ አለፍን ካምና እስከዚህ ድረስ።

ከተከዜ ወዲህ ልቅሶ በረከተ
የትግራይን እንጀ ጦቢያ ግን አለቀ።

ከተከዜ ወዲህ ሳቅ ተሰየፈ
ከተከዜ ወዲህ ደስታ ተሰየፈ
ከተከዜ ወዲህ ሠርግ ተሰየፈ
ከተከዜ ወዲህ በዓል ተሰየፈ
ከተከዜ ወዲህ ትምህርት ተሰየፈ
ከተከዜ ወዲህ መኖር ተሰየፈ።

ከተከዜ ወዲህ ህወሃት ጠነዛ ፤ ህወሃት ቆነሰ
"ኢህአዴግ" ሻገተ ፤ ህወሃት ሸተተ።
ጋላቢው ህወሃት - ብአዴን ኦህዴድን አሞሌ እያላሰ
ደህዴግ ፈረሱ ሀይሌ አስመለሰ
አየር ተበከለ ፤ ጤና ተቃወሰ ፤ ሠላም ደፈረሰ።

የመለስ ነፍስ አባት ሲኞር ገብረመድህን (የሁዋለኛው ጳውሎስ)
ጢሙን እየላገ እጅግ ተደነቀ ፤ እጅግ ተገረመ
ለካስ "ወንጌላዊው" ፤ ለካስ ሀይለማርያም ከርሱም የረቀቀ ሳጥናኤል ነበረ።

የጣሊያኑ ውላጅ የሙሶሎኒ ልጅ መለስ ተበሳጨ፤ በቅናት አረረ
እርሱ የፈጠረው "ወንጌላዊው" ሀይሌ ከርሱም ስለናረ ፤ ከርሱም ስለላቀ።




**ከእንግዲህስ ወዲያ . . . ከእንግዲህስ ወዲያ . . .**

ሀደኮ ኦሮሞ ታጠቂ በገመድ
እማኮ አማራ ታጠቂ በገመድ
ኦጋዴኗም እናት ታጠቂ በገመድ
ኮንሶይቱም እናት ታጠቂ በገመድ
ጋምቤላዋም እናት ታጠቂ በገመድ
እናት ኢትዮጵያ ታጠቂ በገመድ
ልጆችሽን ገዳይ ፋሽስቱን ወያኔ ፤ ናዚስቱን አጋዚ ባንዳውንም ጭምር
ከቤትሽ ለማፅዳት ፤ ከቤትሽ ለመጥረግ
ባነደደው እሳት ራሱን በመማገድ
እራሱን በማንደድ
የብሩህ ቀን ንጋት ነፃነት ለማወጅ !!!

ሀደኮ ኢትዮጵያ እማኮ ኢትዮጵያ እንባሽን አድርቂው
ሀዘንሽን ዋጪው
ክንድሽን አንሺና አንቺ የጀግና እናት
የኮሎኔል ደመቀ የበቀለ ገርባ የሚሊዮኖቹም መሆንሽን አሳይው !!!
በቃ ማለት በቃ መሆኑን አሳይው !!!

************************************ ///// ***********************************************

- ዳውን ዳውን ወያኔ ! መስከረም 22 2009 ዓ/ም (ኦክተበር 2 2016) የህወሃትን መቃብር ቁፋሮ መጠናቀቅ በቅዱሱ የኢሬቻ ኦሮሞ በዓል ላይ ያበሰረውን ጀግና ወጣትና መፈክር በመዘከር በርዕሰነት ተመረጠ። (ፎቶ ከሶሻል ሚዲያ ተገኘ)
- በብሾፍቱ ኢሬቻ በዓል ላይ በፋሽስት ወያኔ እኩይ ጭካኔ ህይወታቸውን ያጡትን ሠማዕታት ደም እንፋረዳለን !!
- በመላው ኢትዮጵያ በሀገር በቀል ቅኝ ገዢ ፋሽስት ወያኔና በባንዳ “ኢህአዴግ” የአገዛዝ ዘመን የደረሰውን ውድመትና ሰቆቃ እንፋረዳለን!!
- ድል ለወጣቱ ትንታግ ትውልድ ትግል !!!
- ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!

ተፃፈ መስከረም 2009 ዓ/ም (ኦክቶበር 2016)
ሲድኒ አውስትራሊያ - mmtessema@gmai.com